ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

Ethiopian Public Health Institute

# በየኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የኖቭል ኮሮና ቫይረስን አስመልክቶ የተዘጋጀ ጋዜጣዊ መግለጫ - የካቲት 3/2012

## ዓለም አቀፍ መረጃ፡

- በዓለም የጤና ድርጅት ሪፖርት መሰረት እስከ የካቲት 3/2012 ይህ መረጃ እስከ ተጠናቀረበት ሰዓት ድረስ ያለው በቫይረሱ የተያዙ ሰዎች ቁጥር አርባሶስት ሺህ አንድ መቶ ስምንት (43,108) ሲሆን ከበሽታው ያገገሙ ሰዎች ቁጥር አራት ሺህ ሃምሳ ሶስት 4053 ሲሆን አንድ ሺህ አስራ ስምን (1018) ሰዎች በቫይረሱ ምክንያት ህይወታቸው አልፏል ። በቫይረሱ የተያዙ ሰዎች በ25 ሀገራት ውስጥ ሪፖርት ተደርጓል።

## ሀገር ዓቀፍ መረጃ

- የቫይረሱን ስርጭት አስመልክቶ እስከ አሁን ድረስ 39 ጥቆማዎች ለኢንስቲትዩቱ የድንገተኛ አደጋዎች ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከል (Emergency Operation Center) ደርሰው በሁሉም ጥቆማዎች ላይ ማጣራት ረደርጓል፣
- 14ቱ የበሽታውን ምልክት ያሳዩ ስለነበረ፣ ተለይተው ወደ ማቆያ ስፍራ (Isolation center) እንዲገቡ ተደርጎ በተደረገ የላብራቶሪ ምርመራ ከቫይረሱ ነፃ መሆናቸውን ከተረጋገጠ በኋላ ወደ ሕብረተሰቡ እንዲቀላቀሉ ተደርጓል፣
- በትላትናው እለት 1ሰው በለይቶ ማቆያ ውስጥ የነበረ ሲሆን በኢንስቲትዩቱ የላብራቶሪ ምርመራ ተደርጎ ውጤቱም ከቫይረሱ ነፃ በመሆኑ ከለይቶ ማቆያ ማእከሉ ወጥቷል። በአሁኑ ሰዓት በለይቶ ማቆያ ማእከል ውስጥ የበሽታው ምልክት ታይቶበት የገባ ሰው የለም።

- ለመገናኛ ብዙሀን ባለሙያዎች፣ ለሆቴል ባለሙያዎችና ከክልልና ከኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ለተውጣጡ ፈጣን ምላሽ ሰጪ ቡድን ስልጠና እየተሰጠ ይገኛል።
- ከቻይና የሚመጡ መንገደኞችን የሙቀት ልየታና የበሽታው ምልክት የታየባቸው መንገደኞችን የጤና ሁኔታ የመከታተል ስራዎች ተጠናክሮ ቀጥሏል።
- በሁሉም የኢንዱስትሪ ፓርክ ባለባቸው ክልሎች ውስጥ የለይቶ ማቆያ ማዕከልና የሕብረተሰብ ጤና አደጋዎች ማስተባበሪያ ማእከላትን ለምላሽ ዝግጁ ለማድረግ በተያዘው እቅድ መሰረት ደቡብ ክልል በሃዋሳ ከተማ ድጋፍ ሰጪ የባለሙያዎች ቡድን በመላክ ከክልሉ ጤና ቢሮ ጋር በመሆን የዝግጅት ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል።
- በአጠቃላይ የኖቭል ኮሮና ቫይረስ ዝግጁነትና ምላሽ እንቅስቃሴ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በሁሉም አቅጣጫ ባሉ የሀገሪቱ መውጫና መግቢያ ድንበሮች ላይ ከጥር 14/2012 እስከ የካቲት 2/2012 ድረስ የኮሮናና የኢቦላ ቫይረስን ዝግጁነት በጋራ በማጣመር ከአንድ መቶ ሰባ ሁለት ሺህ በላይ መንገደኞች ላይ የሙቀት ልየታ ተካሂዷል።

**ጥንቃቄ መደረግ ያለባቸው ጉዳዮች**

- የኖቭል ኮሮና ቫይረስ ከታየባቸው ሀገራት የመጡ መንገደኞች ወይም በዚህ ቫይረስ ከተያዙ ግለሰቦች ጋር ንክኪ የነበራቸው ሰዎች ላይ የበሽታው ምልክቶች (ትኩሳት፤ ሳል፤ የትንፋሽ መቆራረጥ፣ የመተንፈስ ችግር) ከታዩ፣ ማንኛውም የህብረተሰቡ አካል በአስቸኳይ በ8335 ነጻ የስልክ መስመር ላይ በመደወል ሪፖርት እንዲያደርግ እናሳስባለን።
- የበሽታው ምልክት የታየባቸው ሰዎች በሚያስነጥሱበት እና በሚያስሉበት ወቅት አፍና አፍንጫቸውን በሶፍት ወይም በክርን እንዲሸፍኑ፣፤ የተጠቀሙበትን ሶፍት እንዲያቃጥሉ እንዲሁም እጃቸውን በሳሙና በመታጠብ የቫይረሱን ስርጭት እንዲከላከሉ እንመክራለን።
- በተጨማሪም ህብረተሰቡ በሀገራችን እስካአሁን በቫይረሱ መያዙ የተረጋገጠ ሰው አለመኖሩን አውቆ ሳይዘናጋ የበለጠ ጥንቃቄ ኢንዲያደርግ ኢንስቲትዩቱ ያሳስባል።

የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት

አዲስ አበባ

የካቲት/3/2012 ዓ.ም